# ይብላኝ ለወይኒቱ!

አይሆንም እያለች ልሳምሽ ቢኳት፣
አይሆንም እያለች እናግባሽ ቢኳት፣
ስንቱን ሽማግሌ አማጭ ላኩባት፣
መምህሩም በመስቀል ቢያወርዱ ግዝት፣
ቀልድ መሰሎ ታያት እንደ ልጅ ተረት…



ወይ ገዳም ግቢና መንኩሺ በወግ፣
ወይም እንዳርሽ፣ እንድንበላ ሰርግ
ጊዜው ሳያልፍብሽ የትዳር መዓርግ
ወልደሽና ከብደሽ በትዳር፣ በሕግ!
ካልሆነ'ማ አፈር ነሽ፣ ነገ ወደ ፍግ…

ጥፍሯንም በቀለም አሽቀረቀረችው፣
ከንፈሯን በቀለም አሽቀረቀረችው፣
በዕሾኽ፣ በሽቦ ራሷን ያጠረችው፣
መልኳና ውበቷን እንዳፈቀረችው፣
ይብላኝ ለወይኒቱ፣ ቆማ ለቀረችው…

ገ/ኢ. ጐርፉ።